ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ ዓርብ የሚታተም

የትራንስፖርት ዘርፎች ተሸላሚ ‹‹ፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት››

የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በ2005 ዓ.ም ሀምሳ አምስት ተሽከርካሪዎችን ይዞ ለአስር ሺ ሠራተኞች አገልግሎት በመስጠት ሥራ መጀመሩ ይታወሳል። ድርጅቱ ሥራውን ከጀመረበት ወቅት አንስቶ ለመንግሥት ሠራተኛው በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በተለይ የጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ለሚኖሩ ሠራተኞች ከፍተኛ ግልጋሎት እየሰጡ ናቸው። የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት አለም አቀፍ የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓትን በመተግበር በሀገር አቀፍ ደረጃ የትራንስፖርት ዘርፎች ብቸኛው ISO-9001-2015 ሰርተፍኬት ማግኘት በመቻሉ ክቡራን ደንበኞቻችን ጥራት ያለው አገልግሎት ማግኘት በመቻላቸው መሆኑን እናበስራለን። እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ደስ ያለን!!

ድርጅቱ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በፌዴራልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለሚሰሩ ሠራተኞች በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች አገልግሎት ይሰጣል። እንዲሁም ከሥራ መግቢያና መውጪያ ሰዓቶች በውጪ በበዓላትና በእረፍት ቀናት ለሌላው የኅብረተሰብ ክፍል የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በተመጣጣኝ ታሪፍ በመስጠት ወጪውን በመቀነስና ገቢውን በማሳደግ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው አገልግሎቶች በመስጠት ላይ ነው።



ECAE CD

CERTIFICATE

ES ISO 9001:2015

The ECAE CD of the
Ethiopian Conformity Assessment Enterprise
hereby certifies that

Public Service Employees Transport Service Enterprise

Address of Company
Head office: City/Town: Addis Ababa, Sub-City: Lideta, Wereda: 10,
Phone No: +25115155159, Email:psetse2@gmail.com
Branch location: East(Ayat side),West(Jemo site),North(Winget side) and South (kality site)branches in Addis Ababa,Ethiopia.

has established and applied a quality system for

"Transport Service for Employees of Federal and Addis Ababa City Administration, Render a public transport Services for the Society living in Addis Ababa City Administration, Contract Transport Services, Vehicle Maintenance and Inspection."

which conforms to the requirements of the
International Management Systems Standards, ISO 9001:2015

04 Jan. 2022 — Certification Date
03 Jan. 2025 — This certificate is valid until

Certificate Registration number: QS/0094
Issue No. 01, Issue Date: 04 Jan. 2022

Amsalu Enyew
Certification Director
Director, Certification

ENAO
CMS Certification Body CMS0001

Page 1 of 1

ECAE CD
11145 Addis Ababa, Ethiopia
+251 11 646 0548/37
Fax: +251 11 646 0880/81

ድርጅቱ ከሥራ መግቢያና መውጪያ ሰዓቶች ውጭ ለመንግሥት ሠራተኛው በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች አገልግሎት ይሰጣል። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ከፌዴራል ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር በውክልና ተረክቦ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆን፤ ሥራውን የተቀላጠፈና ከብልሹ አሰራር የፀዳ ለማድረግ ሲባል የጠፋ የተበላሸና ምትክ ሰሌዳ የሚፈልጉ ደንበኞች ሰሌዳውን ባወጡበት የትራንስፖርት ቢሮ በኩል መስተናገድ እንዲችሉ ኃላፊነትን ከፌዴራል ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር በውክልና ተረክቦ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆን፤ ሥራውን የተቀላጠፈና ከብልሹ አሰራር የፀዳ ለማድረግ ሲባል የጠፋ የተበላሸና ምትክ ሰሌዳ የሚፈልጉ ደንበኞች ሰሌዳውን ባወጡበት የትራንስፖርት ቢሮ በኩል መስተናገድ እንዲችሉ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። በመሆኑም አገልግሎቱን የምትፈልጉ ደንበኞች ሰሌዳውን ባወጣችሁበት ቢሮ በሕጉ መሠረት አስፈላጊውን መረጃ ይዛችሁ በመቅረብ አገልግሎቱን ማግኘት ትችላላችሁ።

ድርጅቱ ተቋቁሞ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን የተጓዘበትን የዕድገት ደረጃ ስንመለከት በርካታ ስኬቶች እያስመዘገበ በስኬት ላይ ስኬትን እየደረበ በመሄድ ላይ ያለ ድርጅት ነው። ባሳያቸው ከፍተኛ መሻሻሎች በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ጥራት ሽልማት ድርጅት ባካሄደው ውድድር ሦስተኛ ደረጃ የዋንጫ ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል።

በድጋሚ የወጣ የሀገር ውስጥ ግልጽ ጨረታ መለያ ቁጥር 012/2014

አሶሳ ዩኒቨርሲቲ በ2014ዓ.ም የበጀት ዓመት፣

ሎት 1፡-የህትመት ማሽኖች ሙሉ አቅርቦት ግዥ፣ ተከላ፣ ሥልጠና እና ርክክብ (Medium by Printing Machine & their accessories Supply, Installation, training and Commission On tum key Solution) በዘርፉ የተሰማሩ ህጋዊ ድርጅቶች በሀገር ውስጥ ግልጽ ጨረታ ግዥ ዘዴ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት፤

1.የዘመኑ ግብር የከፈሉ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑና የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ በዘርፉ በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ በመንግስት ግዥ/ንብ አስ/ኤጀንሲ ድህረ ገጽ የተመዘገቡ፤ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እና ከግብር ነጻ ስለመሆናቸው ክሊራንስና ሌሎች አስፈላጊ ዶክሜንቶችን ኮፒ አያይዘው ማቅረብ የሚችሉ፡፡

2. ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር መረጃ የያዝውን የጨረታ ሰነድ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ እስከ 16ኛው ቀን 4፡00 ሰዓት ድረስ አዲስ አበባ አዲሱ ገበያ አካባቢ ከፍ ብሎ በሚገኘው አደባባይ ወደ ግራ በመታጠፍ 200 ሜትር ገባ ብሎ እመቤት ሆቴል አጠገብ በሚገኘው የዩኒቨርሲቲው ጉዳይ ማስፈፀሚያ ቢሮ የማይመለስ 200/ሁለት መቶ ብር/ በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የበጀት ሂሳብ ቁጥር 1000021129171 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ በማድረግ የጨረታ ሰነዱን መግዛት (መውሰድ) ይችላሉ።

3. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለሎት1፡-200,000(ሁለት መቶ ሺህ) ብር በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ ወይም ለ120 ቀን የጨረታ ማስከበሪያ በዩኒቨርሲቲው ስም አሰርተው ማስያዝ አለባቸው።

4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን አንድ የህጋዊነትና ቴክኒካል ኦርጅናል እና አንድ የህጋዊነትና ቴክኒካል ኮፒ በተለያየ ፖስታ እንዲሁም አንድ የፋይናንሻል ኦሪጅናል እና እንድ የፋይናንሻል ኮፒ በተለያየ የታሸገ ፖስታ በማድረግ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ አዲስ አበባ አዲሱ ገበያ አካባቢ በሚገኘው የዩኒቨርሲቲው ጉዳይ ማስፈፀሚያ ቢሮ በማቅረብ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 16ኛው ቀን በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር እስከ ጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

5. ጨረታው የሚዘጋው ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ተከታታይ ቀን ተቆጥሮ በ16ኛው ቀን በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በዚሁ ዕለት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4፡15 ሰዓት ላይ አዲስ አበባ አዲሱ ገበያ አከባቢ በሚገኘው የዩኒቨርሲቲው ጉዳይ ማስፈፀሚያ ቢሮ ይከፈታል፡፡ 16ኛው ቀን የበዓል ቀን ከሆነ ወይም የሥራ ቀን ካልሆነ በቀጣይ የሥራ ቀን በተጠቀሰው ቦታና ሰዓት ይከፈታል። ተጫራቾች የፋይናንሻል ዶክመንት የሚጠቀሙት ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው ፎርም ላይ በመሆኑ ዋጋቸውን የሚሞሉት በዚሁ ሰነድ ላይ ይሆናል።

6. አሸናፊ ተጫራቾች የውል ማስከበሪያ ያሸነፉበትን 10% በዩኒቨርሲቲው ስም በማሰራት አሸናፊነታቸው በተገለጸላቸው በ7 ቀናት ውስጥ ውል ባይገቡ ለጨረታ ማስከበሪያነት ያስያዙት ለመንግስት ገቢ ሆኖ ዩኒቨርሲቲው የራሱን አማራጭ ይወስዳል።

7. ተጫራቾች በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ባይገኙ የጨረታውን ሂደት እያስተጓጉልም፡፡

8 ዩኒቨርሲቲው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ መሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

9. አንድ ተጫራች ሌሎች ባቀረቡት ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፡፡

10. የጨረታ ግምገማ ውጤት በውስጥ ማስታወቂያ ይገለጻል፣

11 እሸናፊው ድርጅት ዕቃውን የሚያቀርበው አሶሳ ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀ ቦታ ላይ ይሆናል።

ስለ ጨረታው የበለጠ ማብራሪያ ካስፈለገ በስልክ ቁጥር፡ 0578875014 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል።

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ